# ኢትዮጵያዊነት

ኢትዮጵያዊነት

እያንዳንዱ ሰው የአስተዳደጉ ውጤት ነው። አስተዳደግ ማለት ከቤተሰብ፣ ከአካባቢና ከትምህርት ቤት በተለያየ መጠን የእያንዳንዳችንን ስሜት አስተሳሰብ መንፈስና ማንነት፤ ከሌሎችም ጋር ያለንን ልዩነት ለማነጽ  በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚደረግብን የተጽእኖ ድምር ነው። በአስተዳደግ ውስጥ ትልቁ ኃይል ባህል ነው። ባህል በእያንዳንዳችን ኑሮ ውስጥ ከልደት እስከ መቃብር ያለውን የአንዋንዋር ሥርዓት እርስበእርሳችንና ከሌሎችም ጋር ያለንን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ከፈጣሪም ጋር ያለውን ግንኙነት የሚወስን ነው። ባህል መብልንና አበላልን፣ልብስንና አለባበስን፣ቤትን ከእነዕቃዎቹ፣ንግግርንና አነጋገርን፣ ሀሳብንና አስተሳሰብን፣ጥርጣሬንና እምነትን፣ ስራንና መሳሪያን፣ፍርሃትንና ጉብዝናን፣ፍቅርንና ጥላቻን፣ደስታንና ሐዘንን፤ በአጠቃላይ ኑሮንና ሕይወትን የሚነካ የኅብረተሰብ ቅርስ ነው። በቅርስነቱም ለውጥን የመከላከልና ራሱን የመጠበቅ ዝንባሌ አለው። በአዲሱ ቋንቋ ወግ-አጥባቂ የሚባለው ባህል እንዳይለወጥ፤ ከአባቶች እንደተወረሰ እንዲቆይና ለሚቀጥለውም ትውልድ እንዲተላለፍ የሚታገሉ ሰዎችን ለማመልከት ነው። ድንጋይም ቢሆን በጊዜ ብዛት ይቦረቦራልና ባህልም ጊዜ በሚያጋጥመው ኃይሎች በተለያየ መንገድና በተለያያ ፍጥነት መለወጡ የማይቀር ነው። እንኳን በአንድ አገር ወስጥ ይቅርና በዓለም-አቀፍም ደረጃ የሕዝቦች ባህል ከድሮው ይበልጥ እየተቀራረበ ሲሄድ ይታያል። በልብስም ሆነ በምግብ፣ በአስተሳሰብም ሆነ በስሜት የዓለም ሕዝቦች አውቀውም ሆነ ሳያውቁት በጣም እየተቀራረቡ ነው። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ሕዝብ አሁንም ቢሆን ማንነቱን የሚግልጥባቸውና የሚጠብቅባቸው ሁኔታዎች አሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ባህልን ጠበብ አድርገን ከተመለከትነው ትንሽና ጥቂት የሕዝን ቁጥር ያለው አገር ቢሆንም አንድ ወጥ ሆኖ፤ በሁሉም ነገር ከፋብሪካ እንደወጡ ዕቃዎች አንድ አይነት የሆነ ባህል ለማግኘት አስቸጋሪ ነው። የሰው ልጅ ቆሞ-ቀር አይደለም፤ይዘዋወራል፤ ከሌሎች ጋር ይገናኛል፤ ይማራል፤ በተማረም መጠን ይለወጣል፤ ከዚህም አልፎ ይጋባል፤ ይዋለዳል፤ይዛመዳል።

እንዲሁ በመጀመሪያው የተለያዩ ባህሎች ሆነው የሚታዩት እየቆዩ ይዛመዳሉ። ስለዚህም በእያንዳንዱ አገር ውስጥ በአጠቃላይ የሚታይ ብሔራዊ ባህል አለ። በአሜሪካ ውስጥ ሰሜኑና ደቡቡ፣ምሥራቁና ምዕራቡ የተለያዩ ጠባዮች ቢኖራቸውም በአጠቃላይ ሁሉም የሚለብሱት የአሜሪካ ባህል አላቸው። የስዊትዝርላንድ ሕዝብ ጅርመንኛ፣ ፈረንሳይኛና ኢጣልያንኛ ቋንቋዎችን ቢናገርም ስዊስ የሚያደርገውና ከጀርመኖች፣ከፈረንሳዮችና ከኢጣልያኖች የሚለየው የሲዊስ ባህል አለው።

እንዲሁም ኢትዮጵያ የምትባል አገር አለች። ኢትዮጵያውያን ነን የሚሉ ሰዎችም አሉ። ኢትዮጵያ የሚለው መጠሪያ የፖለቲካ ስም እንጂ ከአንድ የተለየ ኅብረተሰብ፤ ወይም ቋንቋ ወይም ሃይማኖት ጋር የተቆራኘ አይደለም።ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋዎች፣ ብዙ ሃይማኖቶችን የሚከተሉ፣ በተለያዩ የቆላና የደጋ መሬቶች ላይ የተለያየ የኑሮ መሰረት ያሉአቸው ኅብረተሰቦች አገር ናት።

እነዚህ ኅብረተሰቦች በጣም ረጂም በሆነ የታሪክ ዘመን ውስጥ አንዴ ሲጋጩ አንዴ ሲተባበሩ፤ ግን ሳይለያዩ ቆይተዋል። እየተጋቡም፣እየተዋለዱም በጣም ተዛምደዋል። ይህ ለአንዳንድ በዳር አገር ላሉ ኅብረተሰቦች ገና አልሠራም ቢባልም በቁጥር ለሚበዙት ለዋና ዋናዎቹና በደጋው ላይ ለሚኖሩት ኅብረተሰቦች የማያጠራጥር ነው። የኢትዮጵያ ኅብረተሰቦች ሲደባለቁና ሲዛመዱ ባህላቸውም እየተደባለቀና እየተዛመደ ሄደ፤ የቤት አሰራርን ብንመለከት አብዛኛው ተመሳሳይ ነው። በምግብ በኩል እንጀራና ወጥ የማን ነው? ገንፎ የማን ነው? ቅንጨስ? ክትፎስ? ጨጨብሳስ? ቆሎስ? ንፍሮስ? ቆጮስ? አንዳንድ ሰዎች እነዚህን የምግብ ክፍሎች ለተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል ለማደላደል እንደሚቃጣቸው ይገባኛል።

ነገር ግን ቆም ብለው እንዲያስቡበትና እንዲወያዩበት ይጋበዛሉ። በልብስስ ብንሄድ እጀ-ጠባብና ሱሪ፣ኩታ፣ጋቢ፣ቡልኮ የማን የማን ናቸው? ሽሩባና ጎፈሬ የማን ይሆናሉ? ጠላና ጠጅ ለማን ይሰጣሉ? ሞፈሩ፣ቀንበሩ፣ማረሻውና ሌላው የእርሻ መሣሪያ ሁሉ የማን ነው?

ከነዚህም አልፈን ስለተጠራጣሪነትና፣ ስለአትንኩኝ ባይነት፣ ስለ ክብርና ኩራት፣ ስለገበናን መሸፈን፣ ስለይሉኝታ ወዘተ…ብንነጋገርም፣ የዚህ ወይም የዚያ ሳይባሉ የሁሉም ጠባዮች መሆናቸውን ለመገንዘብ እንችላለን። ተስፋን እየተመገቡ መከራን መቻልም የሁሉም ጠባይ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ብዙ የተለያዩ ኅብረተሰቦች የተዋኅዱበት አካል ክፍል መሆን ነው።

ኢትዮጵያዊነት ከጎሠኝነት በላይና ውጭ የሆነ አጠቃላይ ማንነት ነው።

ኢትዮጵያዊነት የዚች ውጥንቅጥ መሬት ባለቤትነት ነው፤ ኢትዮጵያዊነት የደጋው ብርድና የቆላው ሙቀት የሚገናኙበት፤ የደጋው ዝናም ከቆላው ወንዝ ጋር የተዛመደበት ኃይል ነው።

ኢትዮጵያዊነት ለሙሴ፣ለክርስቶስና ለመሐመድ የሚጨሰው ዕጣን በእርገት መጥቆ የሚደባለቅበት እምነት ነው።

ኢትዮጵያዊነት በቁጢማ ጉዝጓዝ ላይ የሚታየው መተሳሰብና መፈቃቀር ነው።

ኢትዮጵያዊነት የአስተዋይነትና፣የሚዛናዊነትና የጨዋነት ባሕርይ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ረዥምና ተፅፎ ያላለቀ  ታሪክ ነው። ብዙ ሰዎች የተሰውለት ስሜት ነው።

ኢትዮጵያዊነት ስቃይና መከራ ነው፤ ኢትዮጵያዊነት ኩራትና ክብርም ነው።

ኢትዮጵያዊነት ጭቆናና ጥቃት ነው፡ ኢትዮጵያዊነት አሻፈረኝና እምቢ ባይነትም ነው።

የኢትዮጵያዊነት ዓላማ ያለችውንና የኖረቺውን ኢትዮጵያን እንደገና ለመፍጠር አይደለም። የኢትዮጵያዊነት ዓለማ ለኢትዮጵያውያን በሙሉ  የሚስማማ እድገታቸውንም የሚያፋጥንና፣ ኅብረተሰባቸውን የሚያጠነክር ሥርዓት መፍጠር ነው። የኢትዮጵያዊነት ችግር ኢትዮጵያ አይደለችም፤ ችግሩ የሥርዓት ችግር ነው። የቤቱ መቃጠል ለትኋኑ በጀኝ እንዳለው ቂል እንዳንሆን።

ኢትዮጵያዊነትን መካድ የራስን ማነንት መካድ ብቻ አይደለም። አባቶችንና እናቶችን፣ ቅደመ-አያቶችን ከነቅርሳቸው መካድ ነው።

በእንደዚህ ዓይነቱ ክህደት ላይ የተመሠረተ ማንነት የት ይደርሳል? ከበሽታ በቀር ትርፉ ምን ይሆናል? ክህደት ራሱን የቻለ በሽታ ሲሆን ማሳካድ ደግሞ የባሰ ነው። ክዶ ማስካድ ታምሜአለሁ፣ ታመሙ እንደማለት ነው። አስታማሚ እንኳን እንዳይገኝ የማድረጉ ጥረት የበሽታውን ምለዓትና ጽናት ያመለክታል።

ሆኖም የኢትዮጵያ ታሪክ ሊያስተምረን እንደሚችለው ኢትዮጵያዊነት እንደላስቲክ ነው። ሲስቡት ይሳባል። ሲለቅቁት ይሰበሰባል። ማለት-ይሳብና ይሳሳል እንጂ አይበጥስም።

---

ምንጭ፤ ኢትዮጵያ ከየት ወዴት፤ መስፍን ወልደ ማርያም፤ 1986 ገፅ፤ 30-32.